## ከመድሎ የነጻ የፖሊሲ መግለጫ (Nondiscrimination Statement of Policy)

የስቴትና የፌድራል የሲቪል መብቶች ህጎችን (state and federal Civil Rights laws) ባከበረ መልኩ የሳንታ ክላራ ቫሊ ትራንስፖርቴሽን ባለስልጣን (Santa Clara Valley Transportation Agency (VTA)) ማንም ሰው በዘሩ፣ በቆዳ ቀለሙ፣ በሀይማኖቱ፣ በመጣበት ሀገር፤ በጎሳው፣ በእድሜው፣ ባለበት አካል ጉዳት፣ በጾታ፣ በወሲብ ዝንባሌው ወይም ስነባህሪው መነሻነት VTA በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ተሳታፊ ሳይሆን እንዳይቀር ወይም የVTA ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች ወይም ተግባራትን በሚጠቀምበት ወቅት ምንም አይነት መድሎ እንዳይደርስበት ለማረጋገጥ ይሰራል።

## በአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካዊያን ደንብ ስር የሰፈረ ማስታወቂያ (Notice under the Americans with Disabilities Act)
## የሳንታ ክላራ ቫሊ ትራንስፖርቴሽን ባለስልጣን (Santa Clara Valley Transportation Agency)

በ1990 በወጣው የአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካዊያን ደንብ (Americans with Disabilities Act of 1990 (“ADA”)ውስጥ በተገለጸው መሰረት የሳንታ ክላራ ቫሊ ትራንስፖርቴሽን ባለስልጣን (Santa Clara Valley Transportation Agency (VTA) መስፈርት የሚያሟሉ አካል ጉዳተኞች በሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ውስጥ ባለባቸው የአካል ጉዳት መነሻነት ተሳታፊ እንዳይሆኑ መድሎ አያደርግም።

**የስራ ቅጥር (Employment) ፦** VTA አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በስራ ቅጥር ወቅት ምንም አይነት መድሎ የማያደርግ ሲሆን በአሜሪካን የእኩል ቅጥር እድል ኮሚሽን (U.S. Equal Employment Opportunity Commission) አማካኝነት የወጡትን መተዳደሪያ ደንቦች ሁሉ ያከብራል።

**የተሳለጠ ግንኙነት (Effective Communication)፦** VTA በአጠቃላይ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት መስፈርት የሚያሟሉ አካል ጉዳተኞች ከVTA ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና ተግባራት እኩል ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችሉና ከሌሎች ጋር የተሳለጠ ግንኙነት ለማድረግ ይችሉ ዘንድ አስፈላጊ የሆነ እርዳታና አገልግሎት ይሰጣል፣ እርዳታ እና አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ዘርፎች መካከል ብቁ የሆኑ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች፤ በብሬል የተዘጋጁ ሰነዶች እንዲሁም መናገር፣ መስማት እና ማየት የተሳናቸው ሰዎች ከሌሎች ጋር የተሳለጠ ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ሌሎች ድጋፎች ይሰጣል።

**በፖሊሲዎችና በአሰራሮች ላይ የሚደረግ ማሻሻያ (Modification to Policies and Procedures)፦** የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ከፕሮግራሞቹ፣ አገልግሎሎቹ እና ተግባራቱ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል VTA አሳማኝ በሆነበት ወቅት ሁሉ በፖሊሲዎቹና በፕሮግራሞቹ ላይ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ያደርጋል። ለምሳሌ ያህል የቤት እንስሳት በፍጹም እንዳይገቡ በተከለከለበት ሁኔታ ውስጥም ቢሆን VTA አገልግሎት ሰጪ እንስሳት ወደተሽከርካሪዎቹ፣ የትራንስፖርት መስጫ መሰረተ ልማቶቹ እና የአስተዳደር ቢሮዎቹ እንዲገቡ ይፈቅዳል።
የተሳለጠ ግንኙነት ለማድረግ ተጨማሪ እርዳታ ወይም አገልግሎት የሚፈልግ ወይም በVTA ፕሮግራም፣ አገልግሎት ወይም ተግባር ላይ ለመሳተፍ እንዲችል በፖሊሲዎች ወይም አሰራሮች ላይ ምክንያታዊ ማሻሻያ እንዲደረግ ለመጠየቅ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚከተለው አድራሻ ግንኙነት መፍጠር ይችላል፦
የ*ADA ሕ*ስተባባሪ (ADA Coordinator)

የዳይቨርሲቲና ኢንክሉዥን ቢሮ (Office of Diversity and Inclusion)
3331 North First Street, B1
San Jose, CA 95134
(408) 321-2300
www.vta.org

እባክዎ በተቻልዎ ፍጥነት የጊዜ ሰሌዳ ከተያዘለት ክስተት 72 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የADA አስተባባሪን (ADA Coordinator) ለማግኘት ይሞክሩ።
ADA በ VTA ፕሮግራም ወይም አገልግሎቶች ተፈጥሮ ላይ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጡ ወይም ከፍተኛ የገንዘብ እና የአስተዳደር ጫና የሚያስከትሉ ለውጦችን VTA እንዲያደርግ አያዝም።

የ VTA ፕሮግራም፣ አገልግሎት ወይም ተግባር አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች አመቺ አይደለም የሚል ቅሬታ ለVTA የADA አስተባባሪ (ADA Coordinator) (VTA's ADA Coordinator) መቅረብ ይኖርበታል(አድራሻው ከላይ ተገልጿል)።
VTA የአካል ጉዳት ላለበት ሰው ወይም ቡድን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ሲል በሚሰጠው ተጨማሪ እርዳታ/አገልሎቶች ላይ ለሚያደርገው ምክንያታዊ ማሻሻያ ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን ምንም አይነት ክፍያ አይጠይቅም። ለምሳሌ ለብዙው ሰው አመቺ ነገር ግን ተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚ ለሆነ ሰው አመቺ ካልሆኑ ቦታዎች እቃዎችን ማምጣት።